# ተሰፍሮ መለካት

አዲስ አማርኛ ፣ ከወዳራት ኪሎ
በጎጠኞች መንደር ፣ ተንጓሎ ተንጓሎ
እኛ ዘንድ ደረሰ ፣ በንፋሱ ታዝሎ
ሲዘመር ሰማነው ፣ መተካካት ብሎ ።

እንደ ቃሉ ትርጉም ፣ ቀላል አማርኛ
እንደነሱ ቀመር ፣ በነሱ ሴረኛ
መተካካት ሳይሆን ፣ ጓደኛን ጓደኛ
ሻግቶ የበሰበሰን ፣ መሸኘት ነው ለኛ ።

ያረጀ ያፈጀን ፣ ስርአት ቀርፍቶ
በዘር በሃይማኖት ፣ መከፋፈል ቀርቶ
አፓርታይድ ጎጠኛ ፣ ከመቃብር ገብቶ
የሕዝቡ አላማ ፣ ምኞቱ ተሳክቶ
የወያኔ ቡድን ፣ ባፍጢሙ ተደፍቶ
መተካካት ይላል ፣ ያኔ አፉን ሞልቶ ።

በወያኔ መዝሙር ፣ የስጥ መተካካት
ትርጉም የሌላቸው ፣ ቃላትን መከካት
በተበላ እቁብ ፣ አላማን ማሳካት
እራስ ከመሸንገል ፣ እራስን ከማርካት
የዘለለ አይሆንም ፣ ላይጋገር ማቡካት ።

ሃያ ሰባት ዓመት ፣ ጥላቻ ነግደው
ሐገርና ሕዝብን ፣ በታሪክ አዋርደው
ከሰፈሩበት ቆጥ ፣ ሳይወዱ ተሳደው
ከነ ጥላቻቸው ፣ እንጦሮንጦስ ወርደው
በሕዝቡ ማዕበል ፣ ከእሳት ተማግደው
ተንጨርጭረው ሲያልቁ ፣ እንደከሰል ነደው
እንተካካለን ፣ ሳይወዱ ተገደው ።

ሕዝቡን የቀየደው ፣ ሲሰበር ሰንሰለት
ሃሰት ስትቀበር ፣ ስትተካ በውነት
አገር ነፃ ስትሆን ፣ ሲታወጅ አርነት
ዘረኝነት ወድሞ ፣ ነግሶ ኢትዮጵያዊነት
ያን ጊዜ ይሆናል ፣ መተካካት በውነት ።

በግፍ ማሰቃየት ፣ በግፍ ሰውን መግደል
አጋሰሱ ሁሉ ፣ የወያኔ ጠብደል
ፍርደገምድል ዳኛ ፣ ሳይጨመር ገደል
ዛር ሲሞትባቸው ፣ ባፍ ጁዶ መደለል
በዋዛ አይረሳም ፣ ያደረሱት በደል
የሚሸወድ የለም ፣ በቃላት በፊደል ።

ንፁሃን ከወህኒ ፣ ከእስር ሳይፈቱ
ካልተረጋገጠ ፣ የህዝባችን መብቱ
በተራ እነሃጎስ ፣ ወደዚያ ሳይዘምቱ
እነሱም እንደኛ ፣ ቀስ በቀስ ሳይሞቱ
አልሰራም ማለት ነው ፣ ከሽፏል መድሃኒቱ ።

እንዳይቆረፍዱ ፣ ከውሃ ውስጥ ነክሮ
ሙዚቃው እንዲያምር ፣ ደህና አርጎ ወጥሮ
ጅማቱን ለክራር ፣ ቆዳውን ከበሮ
አበጃጅቶ ሰርቶ ፣ ጥፍር አርጎ አስሮ
በፈለጉት ቋንቋ ፣ የሚጥም ለጆሮ
ዘፈን ካላሰሙን ፣ በዋይታና እሮሮ
የሚያሽልብ የለም ፣ የሚተኛ አድሮ
መተካካት ያሏት ፣ ቁርጥ ናት ዘንድሮ ።

ጭፈራው ሲደራ ፣ ቂሊንጦ ቃሊቲ
አገር ቀውጢ ስትሆን ፣ በነሃጎስ ፓርቲ
ሲዘሉ እንደፌንጣ ፣ ሲሉ ወይ መዓልቲ
በምናባችሁ ላይ ፣ ሳል አድርጉት እስቲ
መዓዛ ሽቶ አለው ፣ ግሩም እንደ አሪቲ ።

መተካካት ማለት ፣ በወገን እይታ
ሌላም ትርጉም የላት ፣ እቺ ናት ጨዋታ
ዘውዱ ጎፈር ሲሆን ፣ ዘመን ተከርብታ
ጮቤ የሚረገጠው ፣ የሚገኝ እርካታ ።

እቺ ናት እንግዲህ ፣ ያሏት መተካካት
የማይነካውን ፣ ግምኛ በመንካት
አንተ እንዳመጣኸው ፣ አንተ እንደወደድካት
በሰፈሩት ቁና ፣ ተሰፍሮ መለካት ።

ታዛቢው
January 12, 2018